# ግልጽ ደብዳቤ ለአቶ ሰለሞን ገብረስላሴ

ይታይህ እውነቱ

በቅድሚያ ላቀርብልዎ የምፈልገው ምንም እንኳን በዕድሜ ታናሽዎ ብሆንም ስለእርስዎ በበቂ የማውቅ መሆኔን ነው ። በቅርቡ በአውስትራሊያ ራዲዮ የአማርኛ አገልግሎት ለደርጉ መቶ አለቃና የደህንነት አባል ካሳሁን ሰቦቃ የሰጡትን ቃለ መጠይቅ ስሰማ ግን በውን እኔ ስለእርሶ አውቅ ነበርን? ብዬ ራሴን እንድጠይቅና እንድወቅስ አድርጎኛል ።

እኔ ሳውቅ እርሶ የኢሕአፓ አባል ነበሩ ። ከዚያም በሂደት ከሜዳ ከተበተኑት አንዱ መሆን ብቻ ሳይሆን ከክፍሉ ታደሰና ሌሎችም ጋር ሆነው ብተና የተባለውን እንደጠነሰሱና እንደመሩም ሰምተናል ። ሞት ለኢሕአፓ ባይ ። ውሎ ሳያድር ወደ አሜሪካ ከዘለቁ በኋላ እንደገና ወደ ድርጅቱ መመለስዎን ሰማን ። እሰየው ብለን ነበር ። ኢሕአፓም አሁን ሲታይ ሞኝነቱ የሆነውን መሀሪና ቻይ ብለን አድንቀነው ነበር ። እርስዎ ቤተሰብ መስርተው በምቾት ሲኖሩ ኢሕአፓዎች ትግሉን ቀጥለው ስለደረሰባቸው መከራና ጥቃት ያዉቁታልና ብዙ አልልም ። ጓዶች ያሏቸው እነ ጸጋዬ ደብተራው፤ ስጦታው፤ ገብሬ፤ ይስሓቅ፤ ወዘተ ወያኔ እጅ ወድቀው ሰማዕት ሆነዋል ። ይህም ሊያቃጥሎትና ሊያናድዶት በተገባ ነበር፡፡ ይሁን ማአሌሽ ሱዳነ እንል እንደነበረው ተበትነን ሁላችንም ተደናግረን ነበርነ ። ድርጅትዎ መልሶና አቅፎ ብቻ ሳይሆን ለአመራር አድርስዎት ሳለ አመል እንበለውና ዳግም አፍራሽ በተባለ ጎዳና መጭ ማለትዎን ሰማነ። እርስዎ በእንግሊዝኛ መጽሃፍዎ እንዳቀረቡት ለወያኔ አፊዳቪት የሚለውን (የዘረኛ ህጉን ተቀብሎ፤ሁለገብ ትግልን አውግዞ፤ወዘተ) ስምምነት እንጠይቀው የሚለውን የተስፋ ቆራጭ አቅዋም እንቀበል ብለው እነ አቶ መርሻና ዶክተር ጌታቸው በጋሸው ሲነሱ ዋና ደጋፊ ሆነው ከድርጅት ጉባኤ በውድቅት ሌሊት የሄደውን መርሻን በጠዋት ማጀባችሁንና መኮብለላችሁን ሰምተን አዘነ ። ታሪካዊ ስህተት ። ለአቅዋማችሁ በጉባኤ ተገኝታችሁ በመከራከር ፈንታ ሩጣችሁና ተሸቀዳድማችሁ ድርጅታችሁን በማሳጣት በየሚዲያ ተብዬው ተጣዳችሁ። ብዙዎቻችንም ታዘብናችሁ። ለእንደኔ ዓይነቱ ከቀድሞ ስለምናውቃችሁ በአጭር ጊዜ ተሰነጣጥቃችሁ ድራማ እንደምታሳዩን ገምተን ነበርነ። የተወራረዱም አልጠፉም። አልፎም ተሰምቶና ታይቶ በማይታወቅ ሂደት ራሳችሁን ኢሕአፓ (ዴ) በሚል ተሰይማችሁ የድርጅቱ ተጻራሪ ሆናችሁ ብቅ ብላችሁ በደርጎችና ወያኔዎች ሳይቀር ምስጋና አግኝታችሁ ተተራመሳችሁ። በውጭ ሆነን ያየነው ሊኖራችሁ የሚችል ልዩነትና ተቃውሞን ለማዳመጥ ዝግጁ ብንሆንም ድርጊታችሁና ስምሪታችሁ አልዋጥ አሉን ።

ባለፈው በጋ በተደረገው የአሜሪካ የናንተ የ "ዴ" ዎች ጉባኤ እርምት ይምጣ የማለት ወይም የማምጣት ድፍረት ጠፍቶት በነበረው በመቀጠሉ ተስማምተው ራስዎን የኢሕ አፓ (ዴ) አመራርኛ ቃል አቀባይ ብለው ብቅ አሉ ። እውነቱን ልናገርና እርስዎ አቶ ሰለሞን የለየሎት አድርባይ ኖት። ፈሪ ብሎትም አግባብ አለው ። እውነትን መያዝ መጨበጥና እውነትን ለማስተጋባት አልቻሉም ።አንድን ግለሰብ ፈርተው የሚነብጡ ሆነው ነው ያገኘሆት ። ለአውስትራሊያውም ቱሪናፋ ሆነ ራሱን ኢሳት ለሚለው ዋሾ በተደጋጋሚ ቃለ መጠይቅ ሰጥተው ራስዎን አስገምተዋል ። ምንኛ ኢሕአፓን ቢጠሉ ነው ብዬ ራሴን እንደጠይቅ ተገድጃለሁ ። ስከታትል ስቆይ እርስዎ አዋቂ፤ሚዛናዊ፤ ብልህና ብቁ ምሁር የመባል ፍላጎት አንዳልዎ ለመረዳት ችያለሁ ። ይህ ባይሆንማ ኖሮ ፍስሐ ደስታ የተባለን ወንጀለኛ ባደነቁት ልክ ባወገዙት ነበር ። ወገን ፤ሀገር፤ ጓዶች ያሉትን ሁሉ ብለው የተናገሩትን ሁሉ ርባና ቢስ አድርጎታል ። የቀረበብዎት ሂሶች ሁሉ ትክክል ሆነዋል ። የፍስሐ ደስታ መጽሃፍ የደርግ ሽብርተኛ መጽሃፍ ነው አራት ነጥብ። እኒህ ሰው ሳያነቡ ይሆን አድናቆት ያቀረቡት? የሚል ጥያዜ ቢነሳ አይገርመኝም ። መድረክ ማጣበብ ከሚፈልጉት አንዱ ሆነዋልና ። ከዕለታት አንድ ቀን የዚያ ድርጅት አባል ከነበሩ ፍስሃ ደስታን አንቱ ብለው አመስግነው፤ ሚዛናዊ ግምገማ አቀረበ ብለው ሊጽፉ ባልቻሉ ነበር ። ግን ታሪከዎ እንደሚያሳየው ዋናው ችግርዎ ጻረ ኢሕአፓነት የሆነ ይመስለኛል ። ኢሕአፓ "ዴ" ነን ብለው የተሻለ ገጽታ ሊሰጡ የሚከጅሉትም ይህን አቅዋምዎን እንዴት እንደሚቀበሉ ይገርመኛል ። እንደ እርስዎ ጻረ ኢሕአፓ ካልሆኑ !

ለመሆኑ ታሪክ ጻፍኩ ባዩ ፍስሃ ደስታ ማነው ? ያዉቁታል? ዋናው ነፍሰ ገዳይ ደርግ አልነበረም ? በጻፈው መጽሃፍ ምን አለ? የደርግን ወንጀል በሞላ የኢሕአፓ ነው ሊል የቃጣ አይደል? ከወያኔ ጋር በዘረኝነት ጥሩ ግንኙነትን መስርቶ ትጥቅ እስከማስቀረብ የነበረ አይደለምን ? ለሰራተኞች ቀን የሺዎችን የደርግ ፍጅት ክዶ ኢሕአፓን ሊከስ የጻፈ አይደለምን ? እርስዎ ጓዶች የሚሏቸውንም እርምጃ ይወስድባቸው ይገደሉ ብሎ የፈረመና ያዘዘ አይደለምን ? ማንም ሰው-- ይቅር ኢሕአፓ የነበር --ፍስሓ ደስታን ሊያደንቅ፤ ሊያመሰግን፤ ሊደግፍ የሚጠበቅ አይደለም ። አፈርንብዎት አቶ ሰለሞን ። የደርግን ወንጀለኛ ሲያወድሱ ። ጓዶች ይሏቸው የነበሩትን ያስፈጀውን ሲያመስግኑ ። በበኩሌ አንቅሬ ተፍቼታለሁ ። ርኩስ ኖት። ከሀዲ፤በታኝ አንጃ ያሉዎት ሁሉ ቀድመው አውቀዎታልና ይቅርታ እጠይቃለሁ ስብዕና አለዎት ብዬ በመገመቴ ። ኢሕአፓ ነኝ እያሉ ( ቢያንስ ለራስዎ) የደርግን

ወንጀለኛ፤ሽብርተኛ ነፍሰ ገዳይ የሚያወድሱ ስለሆነ ታሪክ ይታዘብዎ ። ስምዎም ሰለሞን ገብረስላሴ በከሃዲዎች ዝርዝር መዝገብ የከረፋ ተብሎ የሚሰፍር ይሆናል ። ጥፋቱ የራስዎ ነው ። ከቻሉ ይመኑና ህዝብን በአስቸኳይ ይቅርታ ይጠይቁ ።

ይታይህ እውነቱ